29ኛ ዓመት ቁጥር 27
29th Year No. 27

ባሕር ዳር ሚያዝያ 19 ቀን 2017 ዓ.ም
Bahir Dar, April 27, 2025

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG
of the Amhara National Region Council in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the Auspices of the Council of the Amhara National Region

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 1352.40 ብር
Unit Price Birr 1352.40

ማውጫ	Content
አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፪/፪ሺ፲፯ ዓ.ም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ	Proclamation No. 292/2025 The Amhara National Regional State Administrative Procedure Proclamation

አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፪/፪ሺ፲፯ ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በክልሉ ሕገ-መንግሥት መንግሥታዊ አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበትና ማናቸውም የመንግሥት ባለሥልጣን ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን የተመለከተ በመሆኑ፤

በአስተዳደር ተቋማት የሚሰጡ ውሳኔዎችና የሚወጡ መመሪያዎች በሰዎች መብቶችና ጥቅሞች ላይ የሚያስከትሉትን ውጤት በሕግ መምራትና ለሕግ የሚገዛ መሆኑን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

Proclamation No. 292/2025

A Proclamation Issued to Determine Administrative Procedure of the Amhara National Regional State

WHERE AS, the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Amhara National Regional State Constitutions provide that the conduct of affairs of government is to be transparent, and that any Public Official is held accountable for failure in his duties;

WHERE AS, it is necessary to ensure whether decisions rendered and directives issued by an Administrative Institutions are guided by and comply with the law, thereby to regulate their effects on human rights and interests;

የአስተዳደር ተቋማት የውሳኔ አሰጣጥና የመመሪያ አወጣጥ መርሆዎችና ሥነ-ሥርዓት እንዲሁም በአስተዳደር ውሳኔዎችና መመሪያዎች ቅር የተሰኘ ሰዉ የውሳኔዎቹንና የመመሪያዎቹን ሕጋዊነት በፍርድ ቤት የሚያስመረምርበት ሥርዓት በመደንገግ አስተዳደራዊ ፍትሕን ማስፈን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) (፩) ድንጋጌ ስር በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፪/፪ሺ፲፯ ዓ.ም**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "**ቢሮ**" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ነው፡፡

፪/ "**የአስተዳደር ተቋም**" ማለት በሕግ የተደራጀ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በክልሉ መንግሥት በጀት የሚተዳደር በየደረጃው ያለ ማንኛውም የመንግሥት አስፈፃሚ ተቋም ሲሆን የከተማ እና የገጠር አስተዳደር መምሪያ ወይም ጽሕፈት ቤትን ይጨምራል፡፡

WHERE AS, it is necessary to guarantee administrative justice through providing a system of decision rendering and principles of directive issuance of administrative institutions as well as a system in which a person who is aggrieved by an administrative decisions and directives can get reviewed same by a court;

NOW, THEREFORE, the Amhara National Region Council, pursuant to the power vested in it under Sub-article (3) (1) of Article 49 of the Revised Constitution of the Amhara National Regional State, hereby proclaimed this proclamation.

PART ONE
GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "**The Amhara National Regional State Administrative Procedure Proclamation No. 292/2025**".

2. Definition

Unless the context require otherwise, in this Proclamation:

1/ "**Bureau**" means the Amhara National Regional State Justice Bureau.

2/ "**Administrative Institution**" means any government executive body organized by law and fully or partially administered by the Regional State budget at various levels and it includes both urban and rural administration departments or offices.

፫/ "**መመሪያ**" ማለት ሕግ አውጪው አካል በሚሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት በአስተዳደር ተቋም የሚወጣና በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ውጤት የሚያስከትል የሕግ ሰነድ ሲሆን በሥራ ላይ ያለ መመሪያን የሚያሻሽል ወይም የሚሽር የሕግ ሰነድንም ይጨምራል፡፡

፬/ "**የአስተዳደር ውሳኔ**" ማለት መመሪያ ማውጣትን ሳይጨምር የአስተዳደር ተቋም በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ነው፡፡

፭/ "**ሰው**" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፮/ በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትን ጾታ ይጨምራል፡፡

፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

፩/ ይህ አዋጅ በሁሉም የአስተዳደር ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚመሩ የዐቃቤ ሕግ፣ የፖሊስ እና የማረሚያ ቤት ተግባራት ላይ በደኅንነት ተቋማት ላይ እና የአስተዳዳር ተቋማት የውስጥ ሠራተኞቻቸዉን በተመለከተ በሚያወጡት መመሪያና በሚሰጡት አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም እነዚህ ተቋማት ከዋና ኃላፊነታቸው በተጓዳኝ አገልግሎት የመስጠትና የቁጥጥር ሥራዎችን በተመለከተ መመሪያ ሲያወጡ እና አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ሲወስኑ በዚህ አዋጅ መሠረት ይገዛሉ፡፡

3/ "**Directive**" means a legislative document that is issued by an Administrative Institution based on delegation power granted by the legislative body which affects people's Rights and Interests, and term also includes the amendment or repeal of an already existing directive.

4/ "**Administrative Decision**" means a decision rendered by an Administrative Institution relating to persons rights or interests in its daily functions, excluding issuance of directive.

5/ "**Person**" means any Natural or Juridical person.

6) Any expression in the masculine gender shall include the feminine gender.

3. <u>Scope of Application</u>

1/ This Proclamation is applicable in all administrative institutions.

2/ Without prejudice to what is provided under Sub-article (1) of this Article, this proclamation shall not be applicable to functions of the Public Prosecutor, Police and Correction institutions which are governed by the criminal procedure law nor to directives issued and decisions rendered by administrative institutions concerning their internal employees.

3/ Notwithstanding what is provided under Sub-article (2) of this Article, these institutions shall be governed by this Proclamation while issuing directive and rendering decisions regarding to their service delivery and monitoring tasks besides to their primary responsibilities.

ክፍል ሁለት

የአስተዳደር መመሪያዎች

ንዑስ ክፍል አንድ

መመሪያ ማውጣትን በተመለከተ

፬. መመሪያ ስለማውጣት

፩/ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም በሕግ በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

፪/ የአስተዳደር ተቋም መመሪያ የሚያወጣው በዚህ አዋጅ በተደነገገው ሥነ-ሥርዓት መሠረት ብቻ ነው፡፡

፫/ ማንኛውም ሰዉ መብቱን ወይም ጥቅሙን በሚመለከት የአስተዳደር ተቋሙ መመሪያ ያላወጣ ቢሆንም የአስተዳደር ውሳኔ እንዲሰጠው የመጠየቅ መብት አለው፡፡

፬/ ማንኛዉም የአስተዳደር ተቋም ሊያወጣ የሚገባውን መመሪያ አለማውጣቱ በሕግ በተሰጠው ኃላፊነት ሊሰጥ የሚገባዉን አገልግሎት ወይም አስተዳደራዊ ዉሳኔ ላለመስጠት ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡

፭. መመሪያ ስለሚወጣበት ጊዜ

፩/ ማንኛዉም የአስተዳደር ተቋም ሊያወጣ የሚገባውን መመሪያ አስመልክቶ በእናት ሕጉ መመሪያ እንዲወጣ በአስገዳጅ ሁኔታ በተደነገገ በ፮ (ስድስት) ወራት ጊዜ ውስጥ ማውጣት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአስተዳር ተቋሙ መመሪያ እንዲያወጣ በእናት ሕጉ አስገዳጅ ባልሆነ ሁኔታ በተደነገገ ጊዜ በተገቢው ጊዜ ውስጥ መመሪያውን ማውጣት አለበት፡፡

PART TWO

ADMINISTRATIVE DIRECTIVES

SUB PART ONE

ISSUANCE OF DIRECTIVES

4. Issuance of Directives

1/ Any administrative institution may issue a directive on the basis of power delegated to it by Law.

2/ An adminstrative institution shall issue a directive only through the procedures provided by this Proclamation.

3/ Regarding matters affecting his right or interest, any person has the right to request an administrative decision even though an administrative institution has not issued a directive.

4/ Failure on the part of an adminstarative institution to issue a directive legally empowered shall not be a reason not to give services or an administrative decision it ought to render.

5. Time of Issuance of Directive

1/ Any administrative institution shall issue a directive within six months period of time since its mother law provided to issue a directive mandatorily.

2/ Notwithstanding what is provided under Sub-article (1) of this Article, it shall issue within a reasonable period of time if the mother law is not mandatorily provided to issue a directive of the administrative institution.

፫/ የአስተዳደር ተቋሙ እናት ሕግ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የወጣ ከሆነ እና መመሪያ የማውጣት ድንጋጌው አስገዳጅ በሆነ ጊዜ ይህ አዋጅ በወጣ ፮ (በስድስት) ወራት ውስጥ ማውጣት አለበት፡፡

3/ If the mother law of an administrative institution is issued before the publication of this Proclamation and if it is mandatory, it shall issue within six months period of time since this proclamation is issued.

፮. መመሪያ እንዲወጣ ጥያቄ ስለ ማቅረብ

፩/ ማንኛውም ሰው አንድ የአስተዳደር ተቋም በአንቀፅ ፭ ንዑስ አንቀፅ (፪) ስር በተደነገገው አግባብ መመሪያ ሳያወጣ ቢቀር መመሪያውን እንዲያወጣ በጽሑፍ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

፪/ ጥያቄው የቀረበለት የአስተዳደር ተቋም ፴ (በሠላሳ) የሥራ ቀናት ውስጥ መመሪያውን የማውጣት ሂደት መጀመር ወይም ምክንያቱን በመግለጽ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡

6. Request for Issuance of Directive

1/ Any person may request an administrative institution through written application to issue a direcives, when an admistrative institution failed to issue a directive pursuant to Sub-article (2) of Article 5 of this Proclamation.

2/ An administrative institution which receives a request for Issuance of a directive shall commence the process of issuing a directive within 30 (thirty) days or reject the request, stating its reason.

ንዑስ ክፍል ሁለት

የቅድመ መመሪያ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት

፯. የመመሪያ አወጣጥን የሚመለከት መዝገብ ስለ ማደራጀት

፩/ ማንኛዉም የአስተዳደር ተቋም የሚያወጣውን መመሪያ በተመለከተ የሚከተሉትን የያዘ መዝገብ ማደራጀት አለበት፦

ሀ) በተቋሙ በመታየት ላይ ያለ ረቂቅ መመሪያ ርዕሰ-ጉዳይ እና የመመሪያውን አወጣጥ መርሃ-ግብር፣

ለ) ረቂቅ መመሪያውን በተመለከተ የወጡ ማስታወቂያዎች፣

ሐ) ረቂቅ መመሪያውን በተመለከተ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ እና ፲ መሠረት የተሰበሰቡ አስተያየቶችንና በአስተዳደር ተቋሙ በአስተያየቶቹ ላይ የተወሰዱ አቋሞችን፤

መ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፩ መሠረት የሚወጣ መመሪያ ከመመሪያ አወጣጥ ስነ-ስርዓት ግዴታ ውጭ የሆነበትን ምክንያት፡፡

SUB PART TWO

PROCEDURES BEFORE ISSUANCE OF A DIRECTIVE

7. Organizing Files about the Issuance of a Directive

1/ Any administrative institution, at the time of issuing a directive, shall organize a file containing the following:

A) Main subject matter and steps for its issuance of the draft directive under issuance by the administrative institution;

B) Notices announced in relation to the draft directive;

C) Comments received and stands taken by the administrative institution regarding comments based on Articles 8 and 10 of this Proclamation;

D) The reason why the directive issued persuant to Article 11 of this Proclamation is exempt from the directive issuance procedure obligation.

፪/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደራጀውን መዝገብ መመልከት ወይም አስፈላጊውን ወጪ ሸፍኖ ቅጂውን መውሰድ ይችላል፡፡

፰. ማስታወቂያ ስለ ማዉጣት

የአስተዳደር ተቋሙ መመሪያ ከማውጣቱ በፊት ስለሚያወጣው ረቂቅ መመሪያ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በተቋሙ ድረ-ገጽ ወይም በሌሎች የመገናኛ ብዙኃን የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ ማስታወቂያ ማውጣት አለበት፦

፩/ የመመሪያውን ረቂቅ ለማዘጋጀት መሠረት የሆነውን ሕጋዊ ሥልጣን እና በመመሪያው ስለሚካተቱት ርዕሰ-ጉዳዮች፤

፪/ የረቂቅ መመሪያውን ቅጂ የሚገኝበትን ሁኔታ፤

፫/ በረቂቅ መመሪያው ላይ ሰዎች አስተያየታቸውን መቼ እና እንዴት ሊያቀርቡ እንደሚችሉ፤

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ መሠረት የተደራጀው መዝገብ የትና መቼ ማግኘት እንደሚቻል የሚገልፅ መረጃ፡፡

፱. ረቂቅ መመሪያን ለአስተያየት ስለ መላክ

፩/ የአስተዳደር ተቋም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ በተደነገገው መሠረት ለሕዝብ ያሳወቀውን ረቂቅ መመሪያ ለሚመለከታቸው የአስተዳደር ተቋማትና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ለአስተያየት መላክ አለበት፡፡

፪/ የሚመለከታቸው የአስተዳደር ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በረቂቅ መመሪያው ላይ አስተያየት ካላቸው አስተያየታቸውን ተቋሙ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በጽሑፍ መላክ አለባቸው፡፡ ተቋሙ የሚወስነው የጊዜ ገደብ በማናቸውም ሁኔታ ከ፲፭ (አስራ አምስት) የሥራ ቀናት ማነስ የለበትም፡፡

2/ Any person can access the files organized under Sub- article 1 of this Article, or obtain a copy by covering the necessary payment of expenses.

8. Noticing

An administrative institution, prior to the issuance of a directive, shall announce a notice on its draft directive on a newspaper with wide circulation or on its website or on any other media, containing the following information:

1/ The legal basis to draft the directive and the subject matters to be covered by the directive;

2/ Indicating where a copy of the draft directive may be accessed;

3/ When and how persons may give comments on the draft directive;

4/ Where and when persons may get access to the file kept pursuant to Article 7 of this proclamation.

9. Soliciting the Draft Directive for Comments

1/ An administrative institution shall solicit the draft directive it has made public, persuant to article 8 of this proclamation, to the concerned administrative institutions and other stakeholders for comments.

2/ Concerned administrative institutions and stakeholders which may have comments on the draft should submit such comments in writing within a time prescribed by the administrative institution. The period for comments to be prescribed by the institution shall not be less than 15 (fifteen) working days in any condition.

፲. የውይይት መድረክ ስለ ማዘጋጀት

፩/ የአስተዳደር ተቋሙ በመመሪያው ረቂቅ ላይ የጽሑፍ አስተያየት መቀበያ ጊዜ ካበቃ በኂላ መመሪያው ከመፅደቁ በፊት ማንኛውም ሰው የሚሳተፍበት የውይይት መድረክ ማዘጋጀትና ግብዓት መሰብሰብ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም በመድረኩ የሚሳተፍ ሰው አስተያየቱን በጽሑፍ ጭምር ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፫/ የአስተዳደር ተቋሙ በሚያዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ አስተያየቶችን ማስተናገድ የሚያስችል በቂ ጊዜ መመደብ አለበት፡፡

፲፩. ሥነ-ሥርዓትን መከተል ስለ ማያስችሉ ሁኔታዎች

፩/ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም መመሪያ ሲያወጣ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፰ እስከ አንቀጽ ፲ ባሉት ድንጋጌዎች ከተመለከቱት ግዴታዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች ነጻ ሊሆን ይችላል፦

ሀ) የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ በመኖሩ በግዴታዎቹ ሥርዓት ውስጥ ለማለፍ ጊዜ የማይፈቅድ ሲሆን፣

ለ) ቅድመ-ማስታወቂያ ማውጣቱ የሕዝብን ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም

ሐ) ቅድመ-ማስታወቂያ ማውጣቱ የመመሪያውን ተፈጻሚነት ፋይዳ ቢስ የሚያደርግ ሲሆን፡፡

፪/ የአስተዳደር ተቋም መመሪያ ሲያወጣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከግዴታ ነጻ እንዲሆን ያደረገውን ምክንያት የያዘ ዝርዝር መግለጫ ማዘጋጀት አለበት፡፡

10. Organizing Discussion Forum

1/ After the expiry date of receiving written comments, the administrative institution shall organize a discusion forum open for all interested persons and collect inputs.

2/ Any person may also submit written comments at the forum discussion.

3/ The administrative institution shall allot enough time for different views to be heard.

11. Conditions that Exempt to Follow Procedures

1/ An administrative institution may be exempted from the obligations provided from under Articles 8 to 10 of this Proclamation where conditions listed hereunder are fulfilled:

A) Where there are conditions of emergencies and time does not allow to go through the obligations;

B) Where the announcement of advance notice may be contrary to public Interest; or

C) Where the announcement of advance notice may superfluous the implementation of the directive.

2/ An administrative institution issuing directives persuant to Sub-article (1) of this Article shall prepare a file explaining the reason justifying the exemption.

ንዑስ ክፍል ሦስት

መመሪያ ስለ ማጽደቅና ስለ ተፈፃሚነቱ

፲፪. መመሪያ ስለ ሚጸድቅበት ጊዜና ሁኔታ

፩/ የአስተዳደር ተቋሙ በተዘጋጀው መመሪያ ረቂቅ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ እና ፲ መሠረት የተወሰነው የጽሑፍ አስተያየት ማቅረቢያና የውይይት መድረክ ማካሄጃ ጊዜ እስኪያልፍ ድረስ መመሪያውን ማጽደቅ አይችልም፡፡

፪/ የአስተዳደር ተቋሙ መመሪያውን ከማጽደቁ በፊት በረቂቁ ላይ የቀረበ አስተያየትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

፫/ የአስተዳደር ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውን ግዴታ ለመወጣት በአስተያየቱ መሠረት ማስተካከያ ማድረግ አለበት ወይም አስተያየቱን የማይቀበል ከሆነ የማይቀበልበትን ምክንያት የሚያብራራ ጽሑፍ ማዘጋጀት አለበት፡፡

፬/ የአስተዳደር ተቋሙ ረቂቅ መመሪያውን ከማጽደቁ በፊት ለአስተያየት ለቢሮው መላክ አለበት፡፡

፭/ ቢሮው በረቂቅ መመሪያው ላይ ያለውን አስተያየት በ፲፭ (አስራ አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ ለአስተዳደር ተቋሙ መላክ አለበት፡፡

፮/ ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስተያየቱን ለመላክ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት መኖሩን አስቀድሞ ለአስተዳደር ተቋሙ በተገኘው የመገናኛ ዘዴ በመግለፅ ለተጨማሪ ተከታታይ ፲፭ (አስራ አምስ ቀናት) ሊያራዝመው ይችላል፡፡

፯/ ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፮) በተቀመጠው ጊዜ አስተያየቱን ሳይልክ የጊዜ ገደብ ካበቃ አስተያየት እንደሌለው ተቆጥሮ መመሪያውን የማጽደቁ ሂደት ይቀጥላል፡፡

SUB PART THREE

RATIFICATION AND EXECUTION OF DIRECTIVES

12. Time and Manner of Ratifying Directive

1/ The administrative institution can not ratify the directive until the expiry date of submission of written comments and discussion forum prescribed under Articles 9 and 10 expire.

2/ The administrative institution shall consider comments submitted on the draft before ratifying the directive.

3/ The administrative institution shall amend the draft in line with the comments or prepare a written justification for rejecting it in fulfilling the obligation indicated under Sub-article (2) of this Article;

4/ The administrative institution shall send the draft to the bureau for its opinion prior to ratificaion of the directive.

5/ The bureau shall submit its opinion to the administrative institution within 15 (fifteen) working days.

6/ Where the bureau fails to submit its opinion within the time prescribed under Sub-article 5 of this Article due to force majeure, it shall notify its adequate reason to the administrative institution through any available means of communication prior to the due date and may postpone the time for another fifteen days.

7/ Where the bureau fails to submit its opinion within the time prescribed under Sub-article 6 of this Article, the process of ratifying the directive shall proceed considered as it does not have opinion on the draft.

፲፫. በመመሪያው ረቂቅና በሚወጣው መመሪያ መካከል ልዩነት ስለመኖር

፩/ የአስተዳደር ተቋሙ በማስታወቂያ ከተመለከተው ረቂቅ መመሪያ ጋር መሠረታዊ ልዩነት ያለው መመሪያ ማዉጣት አይችልም፤ ሆኖም መሠረታዊ ልዩነት ያለው መመሪያ ለማውጣት ከፈለገ የተጀመረውን የመመሪያ አወጣጥ ሂደት በማቋረጥና አዲስ የመመሪያ አወጣጥ ሂደት ከመጀመር አይከለከልም፡፡

፪/ በመጨረሻ መልክ የተዘጋጀ መመሪያ በማስታወቂያ ከተመለከተው የመመሪያው ረቂቅ መሠረታዊ ልዩነት አለው ሊባል የሚችለው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፡-

ሀ) የረቂቅ መመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን በጉልህ የተለወጠ ከሆነ፤ ወይም

ለ) ረቂቅ መመሪያው አዳዲስ ግዴታዎችን አካትቶ የተገኘ ከሆነ፡፡

፲፬. የማብራሪያ ጽሑፍ

ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም መመሪያ በሚያወጣበት ጊዜ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ የመመሪያው ማብራሪያ ማዘጋጀት አለበት፦

፩/ መመሪያው የወጣበት የሕግ መሠረትና ዓላማ፤

፪/ የመመሪያው ይዘት መግለጫ፤

፫/ በማስታወቂያው የተሰራጨው ረቂቅና የመጨረሻ ሆኖ በወጣው መመሪያ መካከል የይዘት ልዩነት ካለ የተደረጉትን ለውጦች ከነምክንያቶቹ የሚገልጽ ማስታወሻ፤

፬/ በረቂቅ መመሪያው ላይ የቀረቡ አስተያየቶችና የተወሰዱ እርምጃዎች ማጠቃለያ፡፡

13. Variance Between the Draft Directive and the Directive to be Issued

1/ An administrative institution can not issue a directive substantially different from the draft announced through notice; however, it is not barred from terminating the process at hand and commence a new one where an institution intends to issue a directive with substantial difference.

2/ A final draft directive shall be considered to be substantially different from the one publicized where:

A) The scope of application of the draft directive has grossly changed; or

B) The draft directive introduces new obligations.

14. Explanatory Statement

At the time of issuing any directive, an administrative institution shall prepare a directive explanatory note containing the following:

1/ Objective and legal basis for issuing the directive;

2/ Explanation of the directive content;

3) Where there are differences of content from the draft circulated through notice and the directive issued, a note explaining the changes and the rationale thereof;

4/ A summary of comments on the draft directive and measures taken in accordance.

፲፭. የመመሪያ ይዘትና ቅርፅ

፩/ በአስተዳደር ተቋም የሚወጣ ማንኛዉም መመሪያ በአማርኛ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በእንግሊዝኛ ቋንቋም ሊዘጋጅ የሚችል ሲሆን ከመመሪያው ዋና ይዘት በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፦

ሀ) የመመሪያው ተራ ቁጥር፤

ለ) መመሪያው እንዲወጣ የሥልጣን ምንጭ የሆነውን ሕግ፤

ሐ) የመመሪያውን አጭር ርእስ፤

መ) ትርጓሜ፣ የተፈፃሚነት ወሰን፣ ዋና ዋና ድንጋጌዎች፤

ሠ) የማሻሻያ፣ መሻሪያ፣ መሸጋገሪያ፣ ማቆያ ድንጋጌ ካለ ይህንኑ የሚመለከት ድንጋጌ፤

ረ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ መመሪያው የጸደቀበትንና ተፈጻሚ የሚሆንበትን ቀን፡፡

፪/ ማንኛውም መመሪያ በአጭርና በግልጽ ቋንቋ መጻፍ አለበት፡፡

፫/ የአስተዳደር ተቋሙ ሌላ ተቋም ያወጣቸውን በሥልጣኑ ክልል የሚወድቁ መመሪያዎች ወይም የሥነ-ሥርዓት ደንቦች በሙሉ ወይም በከፊል በማጣቀስ የራሱ መመሪያ አካል ማድረግ ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የመመሪያው አካል ያደረጋቸውን ሰነዶች ለሕዝብ ተደራሽ ማድረግና በአንቀጽ ፲፮ መሠረት እንዲመዘገብ ለቢሮው መላክ አለበት፡፡

፲፮. የመመሪያ ምዝገባ

፩/ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም መመሪያ እንዳወጣ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው ለቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ አለበት፡፡

15. Content and Form of a Directive

1/ In addition to the substantive body, any directive to be issued by an administrative institution shall be prepared in Amharic language, and as necessary in English language and shall include the following:

A) Serial Number of the directive;

B) Source law of the directive to be issued;

C) Short Title of the directive;

D) Definitions, Scope of Application, Main provisions;

E) Provisions of amendment, revocation, transitory, or saving clauses if any;

F) Notwithstanding the provision of Article 18 of this proclamation, the effective date of the Directive.

2/ Any directive must be written in a precise and clear language.

3/ An administrative institution can incorporate by referring all or part of directives or Code of Conduct which have been issued by another administrative institution where these matters fall within its scope of power.

4/ The Institution shall publicize documents it has incorporated pursuant to Sub-article (3) of this Article and submit copies to the bureau to be registered persuant to Article 16.

16. Registration of a Directive

1/ Any administrative institution after issuing a directive, before put it on force, shall solicit it along with its explanatory statement to the bureau for registration.

፪/ ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የተላከለትን መመሪያ ሕጋዊነቱን፣ መሠረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮ ቁጥር ሰጥቶ ይመዘግባል ወይም የሕጋዊነት ወይም መሠረታዊ መብቶችና መርሆችን የሚጥስ ከሆነ አይመዘግበውም፤ ውጤቱንም ለአስተዳደር ተቋሙ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

፫/ ቢሮው ለምዝገባ የቀረበለትን መመሪያ ከነማብራሪያው መዝግቦ ለአስተዳደር ተቋሙ ካሳወቀበት እለት ጀምሮ ለሕዝብ ክፍት ማድረግ አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበረ መመሪያን ይህ አዋጅ በወጣ በ፩ (አንድ) ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ አለበት፡፡

፲፯. የመመሪያ ተደራሽነት

፩/ ቢሮው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ መሠረት የመዘገበውን መመሪያ በድረ-ገጹ ላይ መጫን አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም ያወጣውን መመሪያ፦

ሀ) አሳትሞ ለሚመለከታቸው መንግሥታዊና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ማሠራጨት፣ እና

ለ) በተቋሙ ድረ-ገጽ ላይ መጫን አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም የመመሪያውን ቅጂ ማግኘት የሚፈልግ ሰው መመሪያውን ባለበት ሁኔታ የመመልከት ወይም ወጪውን ሸፍኖ ከአስተዳደር ተቋሙ የማግኘት መብት አለው፡፡

፲፰. የመመሪያ ተፈጻሚነት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ መሠረት ያልተመዘገበ እና በአንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት በአስተዳደር ተቋሙ ድረ-ገጽ ላይ ያልተጫነ መመሪያ የሕግ ውጤት የለውም፡፡

2/ The bureau shall provide a serial number and register the directive submitted to it persuant to Sub-article (1) of this Article provided that the directive is lawful and does not violate fundamental rights and principles; however, if the Directive is unlawful and violates fundamental rights and principles, it shall not register; and it shall immediately notify the outcome to the administrative institution.

3/ The bureau shall publicize to the public a registered directive with its explanatory statement since the date of registration.

4/ Any administrative institution that had a directive before the promulgation of this Proclamation shall solicit it to the bureau for registration with in a period not exceeding one (1) year from the date of this Proclamation comes into force.

17. Accessibility of Directive

1/ The bureau shall post the directive on its own website that has registered persuant to Article 16 of this Proclamation.

2/ Any administrative institution that Issued a directive shall:

A) Publish and disseminate to Governmental and other stakeholders; and

B) Post it on its website.

3/ Any person who needs to obtain a copy of the directive can access it in its existing condition or may get a copy of it from the administrative institution covering a necessary payment of expenses.

18. Execution of the Directive

1/ A directive that has not been registered persuant to Article 16 of this proclamation and that has not been posted on website of the administrative institution according to alphabetical Letter B, Sub-article (2) of Article 17 shall not have legal effect.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተፈጻሚነቱን ያጣ መመሪያ ተፈፃሚነት እንዲኖረው በዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል ሁለት የተደነገገውን የቅድመ-መመሪያ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ እንደ አዲስ እንዲወጣ ሊደረግ ይገባል፡፡

፲፱. ስለ መመሪያ ተፈጻሚነት ግምገማ

ማንኛዉም የአስተዳደር ተቋም ያወጣውን መመሪያ አፈጻጸም በተመለከተ በየጊዜው እየገመገመ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

ክፍል ሦስት
የአስተዳደር ውሳኔዎች
ንዑስ ክፍል አንድ
የአስተዳደር ውሳኔ አጀማመር

፳. የአስተዳደር ውሳኔ መጀመር

፩/ የአስተዳደር ውሳኔ እንዲሰጥ የሚቀርብ ጥያቄ ጉዳዩ በሚመለከተዉ ሰዉ ወይም በወኪሉ ሊቀርብ ይችላል፡፡

፪/ የአስተዳደር ውሳኔ በሚመለከተዉ የአስተዳደር ተቋም አነሳሽነት ሊጀመር ይችላል፡፡

፳፩. የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ አቀራረብ

፩/ የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ በጽሑፍ ሆኖ እንደሁኔታዉ በአካል፣ በተመዘገበ ፖስታ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊቀርብ ይችላል፡፡

፪/ የአስተዳደር ውሳኔ ይሰጥልኝ ጥያቄ አቤቱታ በጽሑፍ ሲቀርብ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ) ቀን፣ የአቤቱታ አቅራቢው ወይም ወኪሉ ስም፣ ፊርማ እና አድራሻ፤

ለ) አስተዳደራዊ ተግባሩን የሚፈፅመው ተቋም ስም፤

2/ A directive that has lost its validity persuant to Sub-article (1) of this Article may be issued as a new directive following the Procedures provided under Sub-part two of this Part.

19. Evaluation of Execution

Any administrative institution shall periodically evaluate the execution of the directive it has issued and take the necessary measures accordingly.

PART THREE
ADMINISTRATIVE DECISIONS
SUB PART ONE
INITIATION OF ADMINISTRATIVE DECISION

20. Initiation of Administrative Decision

1/ An application for an administrative decision may be submitted by the concerned person or his representative.

2/ An administrative decision may be initiated by the concerned administrative institution.

21. Application of Administrative Decision

1/ An application for administrative decision shall be made in writing, and as the case may be, submitted in person, registered postal address or electronic means.

2/ A written application for administrative decision shall include:

A) Date, name of the applicant or his representative, signiture and address;

B) Name of the institution which executes the administrative act;

ሐ) የአቤቱታ አቅራቢው መብት ወይም ጥቅም፤

መ) ተቋሙ ሊፈፅመው የሚገባ አስተዳደራዊ ተግባር፤

ሠ) ተቋሙ ለሚተገብረው አስተዳደራዊ ተግባር መሠረት የሆኑ ምክንያቶች እና ተያያዥ ማስረጃዎች፡፡

፫/ የአስተዳደር ተቋም የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ የሚቀርብበትን ቅጽ ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

፳፪. ጥያቄን የመቀበል ማረጋገጫ

፩/ አቤቱታ የቀረበለት ተቋም አቤቱታውን በተረከበበት ጊዜ አቤቱታውን የተቀበለ መሆኑን መዝግቦ የማረጋገጫ ጽሑፍ መስጠት አለበት፡፡

፪/ የማረጋገጫ ጽሑፉ አቤቱታውን የተቀበለውን ሰው ስም፣ አቤቱታውን የተቀበለ መሆኑንና ከአቤቱታው ጋር ተያይዘው የቀረቡ ሰነዶችን ዝርዝር የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት

የአስተዳደር ውሳኔ አሰጣጥ መርሆዎች

፳፫. የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠው ሰው

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰው የአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም ሥልጣን የተሰጠዉ የተቋሙ የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ብቻ መሆን አለበት፡፡

፳፬. በሕግ የተሰጠ ሥልጣን ወሰንን አለማለፍ

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ለአስተዳደር ተቋሙ በሕግ የተሰጠውን ሥልጣን ወሰን ማለፍ የለበትም፡፡

፳፭. የግል እና የሕዝብ ጥቅምን ማመዛዘን

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ የአስተዳደር ተቋሙን ተገልጋይ የግል ጥቅም እና በአስተዳደር ተቋሙ ዓላማ የተመለከተውን የሕዝብ ጥቅም ማመዛዘን አለበት፡፡

C) The right or interest of the applicant being sought;

D) Act that the administrative institution has to do;

E) Facts and evidences relevant to administrative decision.

3/ An administrative institution may prepare forms through which an administrative decision application may be submitted.

22. CONFIRMATION OF APPLICATIONS

1/ Upon receiving an application for administrative decision, the administrative institution shall immediately provide a written confirmation.

2/ A written confirmation of application shall contain name of a person who received the application, whether he received the application and details of relevant documents attached therewith.

SUB PART TWO

PRINCIPLES OF ADMINISTRATIVE DECISION RENDERING

23. Administrative Decision Renderer

The person rendering an administrative decision shall be only head of the administrative institution or authorized official or employee of the administrative institution.

24. Respecting Scope of Authority

A person rendering an administrative decision shall respect the scope of authority of the administrative institution established by Law.

25. Balancing of Public and Individual Interests

A person rendering an administrative decision shall balance interest of the applicant with the administrative institution public interest mentioned in its objective(s).

፳፮. አግባብነት በሌለዉ ጉዳይ ወይም ፍላጎት አለመመራት

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ ለጉዳዩ አግባብነት በሌለዉ ጉዳይ ወይም ፍላጎት መመራት የለበትም፡፡

፳፯. ሙያዊ ውሳኔ መስጠት

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ ሙያዉ የሚጠይቀዉን ሥነ-ምግባር፣ ትጋት እና ጥንቃቄ ማክበር አለበት፡፡

፳፰. ማዳመጥ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ መሠረት የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ የአስተዳደር ውሳኔ ከመሥጠቱ በፊት የሚመለከተዉን ሰው ፍሬ ነገር እና ማስረጃ በሚገባ ማዳመጥ እና መመርመር እንዲሁም እንደነገሩ ሁኔታ የሦስተኛ ወገን ተቃዋሚን እና የሕዝብን አስተያየት ማዳመጥ አለበት፡፡

፳፱. በቅን ልቦና መወሰን

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ በቅን ልቦና መወሰን አለበት፡፡

፴. በቂ ምክንያት መስጠት

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ ለአስተዳደር ውሳኔው በቂ ምክንያት መስጠት አለበት፡፡

፴፩. የጥቅም ግጭትን ማስቀረት

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ ከተገልጋዩ ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ከሆነ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የጥቅም ግጭት የሚያስከትልበት ከሆነ ጉዳዩን ከማየት እራሱን ማግለል አለበት፡፡

26. Avoiding Irrelevant Matters or Interests

A person rendering an administrative decision shall not led by irrelevant matters or interests.

27. Rendering Professional Decision

A person who renders an administrative decision shall abide by professional ethical standards and show due diligence and care required by the profession.

28. Hearing

The person rendering an administrative decisions persuant to Article 23 of this Proclamation shall provide adequate opportunity of hearing and investigating to facts and evidence presented by concerned person, and as the case may be, to third party opponent and the public as well.

29. Determing with Good Faith

A person rendering an administrative decisions shall determine with good faith.

30. Reasoned Decision

The person rendering an administrative decisions shall provide adequate reason for the administrative decision.

31. Avoiding Conflict of Interest

Where a person rendering an administrative decision has consanguinity, affinity or any other kind of relation that may cause a conflict of interest, he shall withdraw himself from the case.

፴፪. የተገልጋዮችን እኩልነት ማክበር

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ ሁሉንም ተገልጋዮች በዘር፣ በብሔር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት መጠን፣ በትውልድ ሁኔታ ወይም በሌላ ምክንያት ልዩነት ሳያደርግ መወሰን አለበት፡፡

፴፫. በተገቢዉ ጊዜ መወሰን

፩/ የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ የአስተዳደር ውሳኔዉን ተቋሙ ባስቀመጠው የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ወሰን ጊዜ መሠረት መስጠት እና በጉዳዩ ዙሪያ ያሉ ጥቅሞች በውሳኔው መዘግየት ምክንያት ለጉዳት እንዳይጋለጡ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ የአስተዳደር ውሳኔ ተቋሙ ባስቀመጠው የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ወሰን ጊዜ መሠረት ሳይሰጥ ከቀረ የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄው ውድቅ ተደርጎ እንደተሰጠ ውሳኔ እንዲቆጠር ያደርገዋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ላይ የተደነገገው ቢኖርም አገልግሎት ፈላጊው ማሟላት የሚገባውን ነገር ሳይሟላ በመቅረቱ የሚፈጠር የአስተዳደር ውሳኔ መዘግየት ቢኖር የአስተዳደር ተቋሙ ጥፋት ተደርጎ የሚወሰድ አይሆንም፡፡

፴፬. ተገማች መሆን

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ በፍሬ ነገር ተመሳሳይ የሆኑ ጉዳዮችን በተመሳሳይ ሁኔታ መወሰን አለበት፡፡

፴፭. ግልጽ መሆን

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ ግልጽነትን የተከተለ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡

32. Respecting Clients Equality

A person rendering an administrative decision shall not discriminate between or among clients based on race, ethnicity, color, sex, language, religion, political view, social background, economic class, hereditary status, or any other ground.

33. Timely Decision

1/ The person rendering an administrative decision shall render a decision based on the administrative institution service delivery standard time limit and ensure that interests associated with the decision are not negatively affected as a result of delay.

2/ If an administrative decision is not rendered within the service delivery standard time limit set by the institution, it shall be considered as if the decision is rendered being the administrative decision application rejected.

3/ Notwithstanding what is stipulated under Sub-article (2) of this Article, if the delay in administrative decision is caused because of client failure to fulfill necessary requirements, the delay shall not be considered as fault of the administrative institution.

34. Predictability

The person rendering an administrative decision shall, in matters involving similar facts, render in the same manner.

35. Transparency

A person rendering an administrative decision shall ensure the transparency of the decision making process.

ንዑስ ክፍል ሦስት

አከራካሪ ጉዳይን የመስማት ሂደት

፴፮. ጉዳዩን በሚገባ ስለ መስማት

፩/ ማንኛውም የአስተዳደር ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ጉዳዩ በሚገባ መሰማት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሰው ቢኖርም ጉዳዩን መስማት ሳያስፈልግ ውሳኔ መስጠት የሚቻለው፡-

ሀ) የፍሬ ነገር ክርክር ከሌለ፤

ለ) ልዩ መብት ከሆነ ወይም የአስተዳደር ተቋሙ በሕግ በአማራጭ እንዲወስን ሥልጣኑ ካለው፤ ወይም

ሐ) አስቸኳይ ድርጊት ከሆነ ነው፡፡

፴፯. ጉዳዩ ስለ ሚሰማበት አግባብ

፩/ የአስተዳደር ጉዳይ በሚሰማበት ጊዜ ባለጉዳዩ በክርክሮች ሂደት ሁሉ ተገኝቶ ፡-

ሀ) ምስክርነት የመስጠት፤

ለ) ምስክሮችን እና ሌሎች ማስረጃዎችን የማቅረብ እና የማሰማት፤

ሐ) ለተቋሙ የቀረቡ ማስረጃዎችን የመስማትና የመመርመር መብት አለው፤

፪/ ተቋሙ ማስረጃ ለማግኘት በክርክሩ ተካፋይ ከሆነ ወገን፣ ከምስክሮች፣ ሙያዊ አስረጂ፣ የሰነድ ምርመራ እና ሌሎች ማናቸውንም አስፈላጊ ማስረጃዎችን ለማግኘት ሕጋዊ ዘዴዎችን መጠቀም ይችላል፡፡

፴፰. ስለ መነሣት

፩/ የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጥ ሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ጉዳዩን ከማየት ሊነሣ ይችላል፡-

ሀ) ከጉዳዩ ላይ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ካለው፤

ለ) ባለጉዳዩ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ወይም በቅርብ የሚታወቅ ወዳጁ ሲሆን ወይም የእነዚህ ሰዎች የጥቅም ግጭት ያለበት ጉዳይ ከሆነ፤

SUB PART THREE

HEARING A DEBATABLE CASE

36. Properly Hearing a Case

1/ Any administrative decision shall adequately be heard before it is rendered.

2/ Notwithstanding to Sub-article (1) of this Article, decision may be render without hearing:

A) If there is no arguments of facts of the case;

B) If it is special privilege or if the administrative institution has alternative decision power; or

C) If the issue is urgent.

37. Conditions of Case Hearing

1/ The parties to the case has the right to appear in person and have the right:

A) To give testimony;

B) To present witnesses and produce other evidences;

C) To access and examine evidences presented to the administrative institution;

2/ The administrative institution can use evidences from parties to the case, witnesses, expert witness, documents of investigation and any other legal means to get necessary evidences.

38. Withdrawal

1/ A person may be withdrawn from the administrative decision rendering on one of the grounds listed here under:

A) If he has a direct or indirect interest on the matter;

B) If he has relation with the clients in consanguinity or affinity or intimate relation or if he has conflict of interest with them;

ሐ) በመታየት ላይ ላለው ጉዳይ እንደ ባለሙያ፣ ወኪል ወይም የግል ጠበቃ ሆኖ ተሳትፎ ከሆነ፤

መ) በመታየት ላይ ያለው ጉዳይ ሠራተኛው በስር ውሳኔ አይቶት በይግባኝ የቀረበለት ከሆነ፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከቱ ምክንያቶች ካሉ ውሳኔ በሚሰጠው ሠራተኛ አነሣሽነት ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው አመልካችነት ጉዳዩን ከማየት ሊነሣ ይችላል፡፡

፫/ የይነሣልኝ ጥያቄ ከቀረበና ጥያቄው የቀረበለት ኃላፊ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ እንዲነሣ ጥያቄ የቀረበበት ሠራተኛ ውሳኔ ከመስጠት ሂደቱ ታግዶ ይቆያል፡፡

፬/ የእነሣለሁ ወይም የይነሣልኝ ጥያቄ የቀረበለት ኃላፊ በ፭ (አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ ሠራተኛው ከውሳኔ ሰጪነት እንዲነሣ ወይም እንዲቀጥል መወሰን አለበት፡፡

ንዑስ ክፍል አራት
የአስተዳደር ውሳኔ አፈጻጸም እና እገዳ

፴፱. የአስተዳደር ውሳኔን በጽሑፍ ስለማድረግ

ማንኛውም የአስተዳደር ውሳኔ በጽሑፍ ሆኖ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡-

፩/ የውሳኔ ቀንና ቁጥር፤

፪/ የተቋሙን ስም፤

፫/ የባለጉዳዩን ወይም በክርክሩ ተካፋይ የሆኑ ወገኖችን አድራሻ፤

፬/ የጉዳዩን ወይም አከራካሪ የሆነውን ፍሬ ነገር፤

፭/ የማስረጃዎች ትንተና፤

፮/ የፍሬ ነገር እና የሕግ ትንተና፤

፯/ ውሳኔ፡፡

A) If he has had an involvement on the case at hand as an expert, an agent or a lawyer;

B) If he has rendered a decision on the matter in lower decision.

2/ If there are grounds listed under Sub- article (1) of this Article, the person may be withdrawn from decision rendering process on his own accord, or on petition of an concerned person of the case.

3/ If the withdraw is requested, until the head rendering final decision, an employee against whom the request is made shall remain suspended from entertaining the case.

4/ The head to whom the request of withdrawal is submitted shall render within 5(five) working days whether the employee to be withdrawn or stay.

SUB PART FOUR
ENFORCEMENT OF ADMINISTRATIVE DECISION AND SUSPENSION

39. Making an Administrative Decision in Writing

Any administrative decision shall be made in writing and shall contain:

1/ Date and number of decision;

2/ Name of an administrative institution;

3/ Parties to the case and their address;

4/ The disputed case or matter;

5/ Description of evidences;

6/ Description of fact and law;

7/ Decision.

፵. የአስተዳደር ውሳኔን ለተገልጋዩ ስለመስጠት

ማንኛውም የአስተዳደር ውሳኔ ከነምክንያቱ ለተገልጋዩ በጽሑፍ መሰጠት አለበት፡፡

፵፩. የአስተዳደር ውሳኔን የሚፈጽመው ሰው

ማንኛውም የአስተዳደር ውሳኔ የሚፈጸመው ውሳኔውን በሰጠው ሰዉ ወይም በሚመለከተዉ አካል ይሆናል፡፡

፵፪. የአስተዳደር ውሳኔ እገዳ

፩/ የአስተዳደር ውሳኔ ወዲያውኑ መፈፀም በመብቱ ወይም በጥቅሙ የማይመለስ ጉዳት የሚያደርስበት ሰው ውሳኔው እንዲታገድለት ውሳኔውን ለሰጠው ተቋም አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት አቤቱታ የተቀበለ የአስተዳደር ተቋም እንደየሁኔታው ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ወይም የውሳኔውን ማናቸውም ክፍል ሊያግደው ይችላል፡፡

ንዑስ ክፍል አምስት

በአስተዳደር ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ

፵፫. ቅሬታ የማቅረብ መብት

ማንኛውም ሰዉ በተላለፈበት የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ለአስተዳደር ተቋሙ ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው፡፡

፵፬. የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ማቋቋም

ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም ቋሚ የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ማቋቋም እና ይህንኑ ለተገልጋዮች ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

40. Providing Administrative Decision to Clients

Any administrative decision along with its justification shall be provided to the client in writing.

41. Person to Execute Administrative Decision

Any administrative decision shall be executed by the person or concerned body who has rendered the decision.

42. Suspension of Administrative Decision

1/ A party who may incur irreparable damage on his right and intrerest by immediate execution of the decision, can apply for suspension of the decision to the administrative institution which rendered same.

2/ An administrative institution receiving a petition persuant to Sub-article 1 of this Article, may order the case to be seen again or to suspend any part of the decision as the case maybe.

SUB PART FIVE

COMPLAINT AGAINST ADMINISTRATIVE DECISION

43. Right to Lodge Complaint

Any person against whom an administrative decision is rendered has the right to lodge a complaint to the administrative institution.

44. Establishment of Complaint Handling Body

Any administrative institution shall establish a permanent complaint handling division and notify such establishment to clients.

፵፭. <u>የአስተዳደር ውሳኔው አፈፃፀም መታገድ</u>

ማንኛውም ቅሬታ የቀረበበት የአስተዳደር ውሳኔ ቅሬታው ተመርምሮ እስኪወሰን ድረስ አይፈጸምም፡፡ ሆኖም የውሳኔው ሳይፈጸም መቆየት በሕዝብ ላይ የማይመለስ ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ የአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ዉሳኔዉ እንዲፈጸም ሊያዝዝ ይችላል፡፡

፵፮. <u>ቅሬታውን ስለመመርመርና ስለመወሰን</u>

፩/ የአስተዳደር ተቋሙ የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ቅሬታውን በሚገባ መመርመር እና የዉሳኔ ሐሳብ ለአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም እሱ ለወከለዉ የሥራ ኃላፊ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ የአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም እሱ የወከለዉ የሥራ ኃላፊ በቅሬታ ማስተናገጃ አካል የቀረበለትን የውሳኔ ሐሳብ ተመልክቶ የሰጠው ውሳኔ የተቋሙ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡

፵፯. <u>ውሳኔውን ለተገልጋዩ ስለማሳወቅ</u>

የአስተዳደር ተቋሙ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፮ መሠረት የተሰጠውን ውሳኔ ወዲያዉኑ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ መስጠት አለበት፡፡

<u>ክፍል አራት</u>
<u>በፍርድ ቤት የሚደረግ የአስተዳደር</u>
<u>መመሪያዎችና ውሳኔዎች ክለሳ</u>
<u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>
<u>የክለሳ አጀማመር</u>

፵፰. <u>የክለሳ አቤቱታ ስለማቅረብ</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፮ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

፩/ ማንኛውም ሰው የአስተዳደር መመሪያ በፍርድ ቤት እንዲከለስ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፤

፪/ ማንኛውም በአስተዳደር ውሳኔ ጥቅሙ የተነካበት ሰው ውሳኔው በፍርድ ቤት እንዲከለስ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

45. <u>Suspension of Administrative Decision Execution</u>

Any administrative decision against which complaint is submitted shall not be executed until the complaint is investigated and decided. However, head of the institution may order the decision to be executed where delay in execution may cause an irreparable damage to public.

46. <u>Examination and Decision of the Complaint</u>

1/ The complaint handling body shall properly examine the complaint and present its recommendation to head of the administrative institution or director of work process duly authorized by the Head.

2/ Decision of the head of the administrative institution or director of work process duly authorized by him, after considering recommendation of complaint handling body, shall be considered as final decision of the administrative institution.

47. <u>Notification of Decision to the Party</u>

The administrative institution shall notify the petitioner, in writing, the decision rendered pursuant to Article 46 of this Proclamation.

<u>PART FOUR</u>
<u>JUDICIAL REVIEW OF DIRECTIVES AND ADMINISTRATIVE DECISIONS</u>
<u>SUB-PART ONE</u>
<u>INITIATION OF REVIEW</u>

48. <u>Filing of Petition for Review</u>

Without prejudice to Article 46 of this Proclamation:

1/ Any interested person may file a petition requesting judicial review of a directive;

2/ Anyone whose interest is affected by administrative decision may file petition requesting judicial review.

፵፱. የክለሳ አቤቱታ ስለሚቀርብበት ፍርድ ቤት

፩/ በዞንና ከዞን በታች ባሉ የአስተዳደር ተቋማት የሚሰጥ የአስተዳደር ዉሳኔ እንዲከለስ አቤቱታ የሚቀርበው ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በቢሮና በቢሮ ደረጃ ባሉ የአስተዳደር ተቋማት የሚወሰን የአስተዳደር ውሳኔ እና የአስተዳደር መመሪያ እንዲከለስ አቤቱታ የሚቀርበው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡

፫/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክለሳ አቤቱታዎችን የሚያስተናግድ የአስተዳደር ጉዳይ ችሎት ሊያደራጁ ይችላሉ፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት

የክለሳ መርሆዎች

፶. የክለሳ ምክንያት

፩/ የአስተዳደር መመሪያ በፍርድ ቤት የሚከለሰው:-

ሀ) በአንቀፅ ፲፰ ላይ የተደነገገውን ሳይጨምር በዚህ አዋጅ ክፍል ሁለት የተመለከቱትን የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች ሳይከተል የወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ለ) ከአስተዳደር ተቋሙ የሥልጣን ገደብ ውጪ የወጣ ሲሆን፤ ወይም

ሐ) በእርከን ከመመሪያ በላይ ከሆኑ ሌሎች ሕጎች የሚቃረን ሲሆን ነው፡፡

፪/ የአስተዳደር ውሳኔ በፍርድ ቤት የሚከለሰው በዚህ አዋጅ ክፍል ሦስት የተደነገጉትን መርሆዎች የጣሰ ሲሆን ነው፡፡

49. Jurisdiction to Review

1/ The application of review against an administrative decision rendered by zonal and lower zonal administrative institutions shall be submitted to the regional high courts.

2/ Without prejudice to the provision under Sub-rticle (1) of this Article, the application of review against an administrative decision rendered by bureau and administrative institutions at bureau level shall be submitted to the Regional Supreme Court.

3/ The Regional Supreme and Zonal High Courts may establish special bench dedicated to handle petitions for judicial review of administrative decision.

SUB-PART TWO

PRINCIPLES OF REVIEW

50. Grounds of Review

1/ An administrative directive shall be reviewed by court if:

A) Without including what is provided under Article 18, it was issued without following procedural provisions specified under part two of this proclamation;

B) It is ultravires; or

C) It is contrary to other laws placed higher in the hierarchy of laws.

2/ An administrative decision shall be reviewed by court if it is made in violation of the Principles provided under part three of this proclamation.

፶፩ የክለሳ አቤቱታ የሚቀርበው በመጨረሻ ውሳኔ ላይ ስለመሆኑ

ማንኛውም የፍርድ ቤት ክለሳ አቤቱታ የሚቀርበው የመጨረሻ በሆነ የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ብቻ ነው፡፡

፶፪. አስተዳደራዊ መፍትሔዎችን አሟጦ ስለመጨረስ

፩/ በሕግ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም የአስተዳራዊ ውሳኔ ላይ ለፍርድ ቤት የክለሳ አቤቱታ የሚያቀርብ ባለጉዳይ አቤቱታውን ከማቅረቡ በፊት በአስተዳደር ተቋሙ ውስጥ ያሉትን አስተዳደራዊ መፍትሔዎች አሟጦ መጨረስ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተደነገገው ቢኖርም የአስተዳደር ተቋሙ አስተዳደራዊ መፍትሔ የመስጠቱን ሂደት ተቋሙ ካስቀመጠው የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ወሰን ጊዜ በላይ ያራዘመ እንደሆነ አስተዳደራዊ መፍትሔ አሟጦ መጨረስ ግዴታ አይሆንም፡፡

ንዑስ ክፍል ሦስት
የክለሳ ሥርዓት

፶፫. የክለሳ አቤቱታ የሚቀርብበት ጊዜ

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት የአስተዳደር መመሪያ በፍርድ ቤት እንዲከለስ የሚቀርብ አቤቱታ መመሪያው ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፮ (ስድስት) ወራት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) ወይም (ሐ) መሠረት የአስተዳደር መመሪያ በፍርድ ቤት እንዲከለስ የሚቀርብ አቤቱታ በማናቸውም ጊዜ ሊቀርብ ይችላል፡፡

51. Petition of Review is Submitted on Last Decision

Any judicial review may only be sought against a final decision of an administrative institution.

52. Exhaustion of Administrative Remedies

1/ Unless otherwise provided by law, any applicant for judicial review is required to exhaust all administrative remedies available within the administrative institution before petitioning to court for judicial review.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-article (1) of this Article, exhausting administrative remedies is not mandatory if the process of providing an administrative remedies prolonged the service delivery standard time limit set by administrative institution.

SUB-PART THREE
PROCEDURE OF REVIEW

53. Period of Limitation

1/ A petition to review administrative directive under Sub-article (1), Alphabetical order (A) of Article 50 shall be submitted to a court within 6 (six) months counted after effective date of the directive.

2/ A petition under Sub-article (1), Alphabetical order (B) and (C) of Article 50 of this proclamation can be submitted at any time.

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት የሚቀረብ የክለሳ አቤቱታ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በአስተዳዳር ተቋማት የወጡ መመሪያዎችንም ይጨምራል።

፬/ የአስተዳደር ውሳኔ በፍርድ ቤት እንዲከለስ የሚቀርብ አቤቱታ ባለጉዳዩ የመጨረሻውን የአስተዳደር አካል ውሳኔ እንዲያውቀው ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ፴ (ሰላሳ) ቀናት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት።

፶፬. የጽሑፍ መልስ ስለማቅረብ

የክለሳ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት አቤቱታው ሊመረመር ይገባል ብሎ ሲያምን ቅሬታው የቀረበበት የአስተዳደር ተቋም በ፲፭ (አስራ አምስት) የሥራ ቀናት ዉስጥ የጽሑፍ መልስ እንዲሰጥ ያዝዛል።

፶፭. ሰነዶችን ስለማቅረብ

የክለሳ አቤቱታ የቀረበበት የአስተዳደር ተቋም አቤቱታ የቀረበበትን መመሪያ ወይም ዉሳኔ በተመለከተ አስፈላጊ ሰነዶች እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ሊያዝዝ ይችላል።

ንዑስ ክፍል አራት
የክለሳ ዉሳኔ አሰጣጥ እና አፈፃፀም

፶፮. የክለሳ ዉሳኔ አሰጣጥ

፩/ ፍርድ ቤቱ የክለሳ አቤቱታውን በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥ መርምሮ ዉሳኔ መስጠት አለበት።

፪/ ፍርድ ቤቱ የክለሳ አቤቱታ የቀረበበትን የአስተዳደር መመሪያ ወይም ዉሳኔ ሊያፀና ወይም በሙሉ ወይም በከፊል ሊሽር ይችላል።

፫/ ፍርድ ቤቱ የክለሳ አቤቱታ የቀረበበትን የአስተዳደር መመሪያ ወይም ውሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ሲሽር የአስተዳደር ተቋሙ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ የተጠቆሙ ግድፈቶችን አስተካክሎ መመሪያውን እንደገና እንዲያወጣ ወይም እንዲያሻሽል ወይም ውሳኔ ሰጥቶበት የነበረውን ጉዳይ እንደገና መርምሮ እንዲወስን ሊያዝዘው ይችላል።

3/ A petition submitted based on Sub-article (2) of this Article shall include any directive issued by administrative institutions before publication of this proclamation.

4/ A petition for review of administrative decision to court shall be submitted within 30 (thirty) days to be counted after the applicant was notified of the decision.

54. Submission of Written Response

Where the court finds the petition for review has the merit, it shall order the administrative institution, against which petition of review is submitted, to submit is written response within 15 (Fifteen) working days.

55. Submission of Documents

The court may order an administrative institution, against which review petition is being considered, to submit documents relating to the directive or administrative decision under consideration.

SBU-PART FOUR
DECISION OF JUDICIAL REVIEW AND EXECUTION

56. Judgement of Review

1/ The court, as much as possible, shall investigate the petition of review and render its decision within short period of time.

2/ The court may confirm; or partially or fully reverse the administrative decision or directive submitted for review.

3/ When the court partially or fully reverses the administrative decision or directive submitted to it, it may order the administrative institution to reissue the directive or improve or redicide its administrative decision by rectifying shortcomings identified through the court's decision.

፶፯. የክለሳ ዉሳኔ አፈፃፀም

፩/ በፍርድ ቤት የተሰጠ የአስተዳደር መመሪያን ወይም ዉሳኔን የማፅናት ወይም የመሻር ውሳኔ ወዲያዉኑ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪/ ፍርድ ቤቱ የአስተዳደር መመሪያው ወይም ውሳኔው እንዲሻሻል ካዘዘ የአስተዳደር ተቋሙ በዚህ አዋጅ ክፍል ሁለት እና ሦስት የተመለከቱትን የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች እና መርሆዎች አክብሮ መመሪያውን ወይም የአስተዳደር ውሳኔውን በተገቢዉ ጊዜ ማሻሻል አለበት፡፡

፫/ በፍርድ ቤቱ የተሰጠ የአስተዳደር መመሪያን ወይም ዉሳኔን በሙሉ ወይም በከፊል የመሻር ዉሳኔ ወይም የማሻሻል ትዕዛዝ የክለሳ አቤቱታ የቀረበበትን መመሪያ ወይም ውሳኔ ሕጋዊ ኃይል በሙሉ ወይም በከፊል ያስቀራል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተገለጸው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ አንድን የአስተዳደር መመሪያ በከፊልም ሆነ በሙሉ የሚሽር ውሳኔ ሲሰጥ የአስተዳደር ተቋሙ መመሪያው ከመሻሩ በፊት በተሻረው መመሪያ መሠረት የሰጣቸው የአስተዳደር ውሳኔዎች እንደጸኑ ይቆያሉ፡፡

ክፍል አምስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፶፰. የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ተፈፃሚ ስለመሆኑ

በዚህ አዋጅ ክፍል አራት ባልተመለከቱ የክለሳ ሥነ-ሥርዓት ጉዳዮች ላይ አግባብነት ያላቸዉ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

57. Execution of Review Decision

1/ Decision of the court to confirm or reverse an administrative directive or decision shall be executed immediately.

2/ If the court orders for revision of the administrative directive or decision, the administrative institution shall do the same in appropriate time by giving due consideration to the procedural Provisions provided under part two and three of this proclamation.

3/ Judgement of the court fully or partially reversing a directive or administrative decision, or order of revision shall, either fully or partially, revoke power of legality of such directive or decision.

4/ Notwithstanding the provision of Sub-article (3) of this Article, when the court renders a decision partially or fully revoking an administrative decision, decisions of an administrative institution made on the basis of a revoked directive prior to the ruling of the court shall stay valid.

PART FIVE
MISCELLANEOUS PROVISIONS

58. Applicability of the Civil Procedure Code

On procedural matters of review not covered by Part Four of this Proclamation, the relevant Provisions of the Civil Procedure Code Shall be applicable.

፶፱. የጉዳት ካሣ ስለመጠየቅ

በአስተዳደር ተቋሙ ውሳኔ ወይም አስተዳደር ተቋሙ በሚያወጣው መመሪያ ጥፋት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካሳ እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት አለው፡፡

፷. መረጃ የመስጠት ግዴታ

ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም ከመመሪያ ማውጣት ወይም ከአስተዳደር ውሳኔ መስጠት እና እነዚህን ከመፈጸም ጋር በተያያዘ በሌላ ሕጋዊ አካል ሲጠየቅ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፷፩. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፷፪. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ባሕር ዳር

ሚያዝያ ፲፱ ቀን/፪ሺ፲፯ ዓ.ም

አረጋ ከበደ ለጋስ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዚዳንት

59. Requesting Compensation

Any person who has incurred damage as a result of fault committed by the administrative institution decision or issuance of directives shall have the right to request compensation to be paid in accordance with relevant laws.

60. Obligation to Provide Information

Where any administrative institution is requested by legal organ to provide information relating to issuance or rendering of administrative decisions and execution of such shall have an obligation to provide information.

61. Power to Issue Regulation

The Council of the Regional Government may issue Regulation to implement this Proclamation.

62. Effective Date of the Proclamation

This Proclamation shall enter into force since the date of publication on the Zikre Hig Gazette of the Region.

Done at Bahir Dar,

This 27th date of April, 2025.

Arega Kebede Legas

President of the Amhara National Regional State.